# ወጣቱ ለምን ይደናገራል?

ዘአማን በላይ 03-25-18

ይህ ፀሐፊ ወጣትም ነው፤ አይደለምም። ወጣት እንደሆነ የሚሰማው፣ ‘ከ18 እስከ 35 ዓመት ድረስ’ የሚለውን የሀገራችንን የወጣትነት ክልል ገደብ ስለሚያሟላ ነው። ወጣት አልሆንኩም ብሎ የሚያስበው ደግሞ፣ ከወጣትነት የዕድሜ ጣሪያ ጫፍ ስድስት ቀናቶች ብቻ ስለሚያልፉት ነው። ሆኖም ስሜቱና እሳቤው ከጎልማሳው ይልቅ ለወጣቱ ይቀርባል። ግና ይህ ፀሐፊ ትናንት የዛሬ መሰረት መሆኑን በውል ይገነዘባል። የዚህ ሀገር የፖለቲካ ትኩሳትና አሁን የደረሰበት የጡዘት ደረጃ ያሳስበዋል። ዳሩ ግን ማናቸውም ጉዳዩች ሀገራችን በጠንካራ መሰረት ላይ በገነባቻቸው ተቋሞቿ ፈር እንደሚይዙ ጠንካራ እምነት አለው። ይህ ፀሐፊ ከሀገራችን ከእርሱ ቀደምት ከሆኑና ጥልቅ እሳቤ ካላቸው ታላላቅ ሰዎች እየተማረና በአቅሙ ጥሬውን ከብስሉ እየለየ የመጣ ነው። ለእነዚህ ታላላቅ ሰዎች እነሆ ከመቀመጫው ተነስቶ የአክብሮትና የምስጋና ባርኔጣውን ከፍ አድርጓል።

ይህ ፀሐፊ ባለው ውስን አቅም ለዚህ ሀገር የሚበጀውን ነገር እየለየ፣ ያገኛቸውን ግንዛቤዎች እንደ አቅሙ ከመወረወር አኳያ ራሱን ሲመዝን እዚህ ግባ የሚባል ስራ አለማከናወኑ፤ በእንስራ የቅሬታ ማዕበል ውስጥ ሆኖ እንደ እርጎ እንዲናጥ አድርጎታል። ታዲያ ይህን የቅሬታ ወጀብ ወደ ጎን ብሎ እንደ ዜጋ ያለውን ለማካፈል በተለያዩ የመገናኛ ዘውጎች ‘እኔም ለሀገሬ ሃሳብ አለኝ’ ለማለት ይሞክራል—“ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም” እያለ። “የውሃ ጠብታ እያደር ድንጋይ ይበሳል” የሚለውን የሀገራችንን የሰሜን ሰው ይትብሃል እያስታወሰም ይታትራል። ‘ሀገሬ ለእኔ ምን አደረገችልኝ’ን ትቶ፣ ‘እኔስ ለሀገሬ ምን አደረግኩላት’ የሚለው አባባል እያስታወሰ “ይጠበቅብኛል” ብሎ የሚያምናቸውን የሃሳብ ደርዞችን እየጣለ ያነሳል። ይህ አጭር መጣጥፉም የዚህ ጥረቱ ሽራፊ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

‘እውን ወጣቱን ምን ያደናግረዋል?፣ ለምንስ ተስፋ ይቆርጣል?’—ይህን ጥያቄ በአንክሮ አጢኖ ለመመለስ ብዙ ምርምር የሚጠይቅ አይመስለኝም። በአሁኑ ወቅት የምንገኝበት የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግልፅ ነውና። እንዳልኩት ወጣቱ ከ18 እስከ 35 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የዚህ ስርዓት እንጂ ያልፉት ስርዓት ፍሬ አይደለም። እነዚያን ስርዓት በተገቢው መንገድ ያውቃቸዋል ብዬ

አላስብም። እናም ለምን እንደሚደናገርና ተስፋ እንደሚቆርጥ ለማወቅ ታሪክን በጥቂቱ ሽርፎ የትናንቱን ማስታወስ ያስፈልጋል። ይህም የተሟላ ስዕል ይሰጣል ብዬ አምናለሁ።

ኢትዮጵያ ስር በሰደደ የድህነት አረንቋ ውስጥ ስትዳክር የኖረች ሀገር ናት። ቀደም ባሉት የድህነት ጠባቂና "እሹሩሩ" ባይ ስርዓቶች ውስጥ ተረግጦ የቆየው የሀገሬ ህዝብ፤ በድህነት አረንቋ ውስጥ እየዳከረ 'ኧረ የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ያለህ!' እያለ በየአቅጣጫው ቢጮህም ሰሚ አልነበረውም። ፊውዳላዊና አምባገነናዊ ስርዓቶቹ መስሚያቸው ጥጥ ነበር። እናም በየዕድሜ ዘመናቸው አንዱ 'ስዩመ እግዚሐብሔር ነኝ!' ሲል፣ ሌላው ደግሞ 'የፖለቲካ ጥያቄ የስልጣን ጥያቄ ነው!' በማለት የህዝቡን ሁለንተናዊ ጥያቄዎች በአፈሙዝ አፍኖ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። የህዝቡን ጥያቄዎች ከመመለስ ይልቅ፤ አንዱ ህዝቡን በኃይማኖት ሸብቦ፣ ሌላው ደግሞ በጠብ-መንጃ አፈና ሲገዙትና ሲገዘግዙት መኖራቸው ገሃድ ነው።

ያ ህዝብ ግን በስርዓቶቹ ላይ አመፀ። 'እምቢኝ፣ አልገዛም' አለ። በየመዝገበ ቃላቱ ላይ የድህነት ተምሳሌት ሆኜ ዕድሜ ልኬን እየተጠቀስኩ አልኖርም አለ። ታሪኬን ቀያሬ ራሴ ነኝ ብሎም ተረባረበ። በቅድሚያ 'ሰማይ አይታረስ፣ ንጉስ አይከሰስ' የሚለውን ዘውዳዊ ስርዓት በተባበረ ክንዱ ጣለው። ለጥቆም ትግሉን በጠብ-መንጃ አፈሙዝ የቀማውን ወታደራዊ ጁንታ በያዘው ጠብ-መንጃ ያነጋግረው ጀመር። በተለይ ድህነቱና ሰቆቃው በገነገነበት የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሚገኙ አስር የማይሞሉ ወጣቶች በጣት የሚቆጠሩ ብረቶችን ይዘውና የህዝቦችን የዘመናት ጥያቄዎች አንግበው ዱር ቤቴ አሉ። ትግሉን አጧጧፉት።

ታዲያ ትግሉ ከሰሜን ይጀመር እንጂ፣ የሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ያካተተ ነበር። ሁሉም በየፊናው ደርግን ለመጣል መታተሩን ታሪክ ይነግረናል። መራር፣ እልህ አስጨራሽና ሰው መሆንን የሚያስጠላው ያ የህዝቦች ትግል ስፋት ያለውና ዘለግ ያለ ጊዜን የጠየቀ ነበር። ግና የተከፈለው መስዕዋትነት ተከፍሎ፣ የጎደለው አካል ጎድሎና የወደመው ንብረት ወድሞ፤ በ17 ዓመታት ሁሉን አቀፍ የትግል ርብርብ አዲስ ብርሃን የሀገራችንን ሰማይ እንዲናኘው አደረጉት—እነዚያ ውድ የህዝብ ልጆች፤ ምስጋናቸው ከፍ ይበልና! ኢትዮጵያም በአዲስና በህዝቦች በሚመራ የፖለቲካ ቅያድ ውስጥ ገባች። ሰላምን ፈልጎ፣ ድህነትን ተጠይፎ፣ ነፃነትንና እኩልነትን ሽቶ ብረት ያነሳው የሀገሬ ህዝብ፤ በፈቃዱና በፍላጎቱ የአዲስ ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ባለቤት ሆነ። ይህ ስርዓት በህዝቦች የህይወትና የአካል መስዕዋትነት እንዲሁም ደምና አጥንት ፍላፃ የመጣ ነው። ይህን እውነታ ወጣቱ ቢያንስ የሀገሩን ታሪክ ሲማር

የሚያውቀው ይመስለኛል። የዛሬው ወጣት ከእነዚያ አይበገሬ ቀደምት ወጣቶች ባመቻቹለት ጥርጊያ ላይ የበቀለ ቡቃያ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ይህ ወጣት እዚህ ላይ ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ አዲሱ ፌዴራላዊ ስርዓት እውን ሲሆን ድህነት፣ ኋላ ቀርነትና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች ካለፉት ስርዓቶች ጋር በመንከባለል ዛሬም ድረስ የተከተሉን ቅሪቶች መሆናቸው ነው። ያም ሆኖ "የድህነት ተራራ የሚናደው በዕውቀት ጥይት ነው" እንዲል ባለ ምጡቁ አዕምሮ ባለቤትና ባለ ራዕዩ ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ አስረስ፤ አዲሱ ስርዓት በዋነኛነት መጠነ ሰፊ የሆነውን የሀገራችንን ድህነት በመቅረፍ የህዝቦችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት በየደረጃው የማረጋገጥ ስራዎችን በዕውቀት ላይ ተመስርቶ አከናውኗል፤ እያከናወነም ነው።

አዎ! ስርዓቱ የዛሬው ወጣት ነው። ወጣቱ የስርዓቱን ዕድሜ ያህል ህይወትን ተጉዟል—በአማካይ 26 ዓመታትን። ይህ ወጣት ከ26 ዓመት በፊት እንደነበሩት ወጣቶች በማንነቱም ይሁን በኑሮው አንገቱን ደፍቶ የሚሄድ አይደለም። ዛሬ ቀና ብሎ በማንነቱ በመኩራት እንዲሁም በሀገሪቱ በመመዝገብ ላይ ከሚገኘው ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት በኢኮኖሚው ላይ ባበረከተው አስተዋፅኦ መጠን ተጠቃሚ ሆኖ ወደ አዲስ የለውጥ ምዕራፍ እየገሰገሰ ነው። ለአብነት ያህል፤ ምንም እንኳን ስፋትና ጥልቀቱ እንዲሁም ከአፈፃፀም ጋር በተያያዘ ዕድሉ (opportunity) ገና የሚቀረው ቢሆንም፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በርካታ ወጣቶች በተለያዩ አነስተኛና ጥቃቅን የስራ መስኮች ተደራጅተው ተጠቃሚ ሆነዋል። ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጠቅመው ሀገራቸውን ያሳደጉም ቀላል አይደሉም። ይህም በስርዓቱ ውስጥ ወጣቶች ተጠቃሚነት ስለ መሆናቸው አንድ ማሳያ ይመስለኛል። አዎ! የሀገራችን ወጣት ከስርዓቱ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ አይደለም። ሊሆንም አይችልም—የራሱ ስርዓት መልሶ ራሱን ሊጎዳው አይችልምና።

አንድ ተደማሪ አብነት ማንሳት እችላለሁ። ይኸውም በቅርቡ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር የበጀት ዓመቱን የስምንት ወራት የስራ አፈፃፀሙን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲያቀርብ፤ በያዝነው ዓመት ስምንት ወራት ውስጥ ለ882 ሺህ 200 ወጣቶች የስራ ዕድል መፈጠሩን የተመለከተ ነው። የስራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ከእነዚህ ወጣቶች ውስጥ 546 ሺህ 951 ወጣቶች ቋሚ የሰራ ዕድል አግኝተዋል። ቀሪዎቹ 335 ሺህ 258 ደግሞ ጊዜያዊ ዕድል የተፈጠረላቸው ናቸው። ይህም ከዓመቱ እቅድ 68 በመቶ የሚሸፍን መሆኑ ተወስቷል። በእኔ እምነት ይህ ለወጣቶች የተፈጠረው የስራ ዕድል (Job opportunity) የሚያበረታታ ቢሆንም፤ ሀገር አቀፍ ደረጃ ካለን የወጣት ብዛት አኳያ ሲታይ አጥጋቢ ነው ብሎ መውሰድ የሚቻል አይመስለኝም። ከዚህ በላይ የስራ ዕድል መፍጠር የሚቻል ይመስለኛል። የስራ ፈጠራ ዕድሉን

በማስፋት ወጣቱን ይበልጥ ተጠቃሚ ማድረግም ይቻላል። በተለይ ስራ ፈጠራውን ለማጎልበት መንግስት ለወጣቶች ከመደበው የ10 ቢሊዮን ተዘዋዋሪ ተንቀሳቃሽ ፈንድ ብድር ውስጥ፤ በስምንት ወራት ውስጥ 6 ነጥብ 39 ቢሊየን ብር ብቻ መሰራጨቱ ተገቢ አይመስለኝም። ዝቅተኛ አፈፃፀም ነው። ለዚህም እኔ ራሴ የማውቃቸው ከፈንዱ መመሪያ ውጭ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ወጣቶች ብድሩን እንዳያገኙ የሚደረገው የቢሮክራሲ ማነቆ እና ብድሩን ለማግኘት በፈንዱ መመሪያ ላይ የተቀመጠው 12 ደረጃዎች ያሉት ተስፋ አስቆራጭ የብድር መፍቀጃ ሁኔታ እንዲሁም በክልል አመራሮች የሚታየው ቅድሚያ ለወጣቶች ያለመስጠት ችግሮች በፍጥነት መወገድ ብዬ አምናለሁ። እናም ያለንን ሃብት እንኳን ተጠቅመን ወጣቶች ስራ እንዳይፈጥሩ የሚያደረገውን ይህን ተስፋ አስቆራጭ አሰራር የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት ተቀናጅተው በመስራት የወጣቱን ተስፋ ማለምለም የሚኖርባቸው ይመስለኛል።

ችግሮችን በመፍታት ወጣቱ ተደናግሮ ተስፋ እንዳይቆርጥ ማድረግ ይገባል። የስራ ዕድልን በማስፋት የስርዓቱ ተጠቃሚው ወጣት ስለ ልማት ማሰብ ትቶ አመፅን እንዳይማር ማድረግ ይቻላል። ችግሮቹን በግልፅ ውይይት በማሳየትና የሚፈቱበትን አግባብ በማመለላከት ሁኔታውን መቀየር ወቅታዊ ጉዳይ ይመስለኛል። አሁን የምንገኝበት የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ግልፅ ስለሆነ ‘ይህን መሰል ክስተት ለምን ተፈጠረ?’ ብሎ መጠየቅ የመፍትሔው አካል ሊሆን አይችልም። ከዚህ ይልቅ፤ ለክስተቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑትን ጉዳዩችን መመልከት ጠቃሚ የሚሆን ይመስለኛል። እነርሱም አንድም፣ ባለፉት ዓመታት ውስጥ ኢኮኖሚው ቢያድግም መጠነ ሰፊው ድህነት ከፍተኛ ስለነበር ሁሉንም ማዳረስ አለመቻሉ፤ ሁለትም፣ እገሌ ከእገሌ ሳይባል ሁሉም የሀገራችን ክልሎች ወጣቱን ለመጥቀም የሚያስችሉ ስራዎችን በሚፈለገው መጠን መስራት አለመቻላቸው ነው።

የድህነት ሸክሙ ትልቅ በሆነባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ፣ ችግሩን ሁሉንም አካታች በሆነ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታት አይቻልም—ጊዜን ይጠይቃል። ያም ሆኖ መንግስትና ህዝቡ በድህነት ላይ በከፈቱት ዘመቻ ባለፉት ስርዓቶች የነበረውን የድህነት ሁኔታ በግማሽ ያህል መቀነስ ችለዋል። ርግጥ ነው—እንደ ማንኛውም ሀገር ኢትዮጵያ የአቅም ውስንነት አለባት። ይህም የአቅም ውስንነት የገንዘብ እጥረት ነው። መንግስት ይህን እጥረት በመቆጠብ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ሰርቷል። ይሁን እንጂ እንዳልኩት ከድህነቱ ስፋት አኳያ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ማዳረስ አልተቻለም። ከእነዚህ ውስጥ ወጣቶች ቀዳሚዎቹ ናቸው። ይህ ሁኔታም መደናገርና ተስፋ መቁረጥን (confusion and frustration) አስከትሏል።

“በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ አበው፤ ይህ ችግር ባለበት ሀገር ውስጥ ሁሉም ክልሎች የራሳቸውን የቤት ስራ በሚፈለገው መጠን ባለመስራታቸው ሁኔታውን አባብሶታል። ምንም እንኳን ሀገራችን የገንዘብ እጥረት ቢኖርባትም፣ በክልል አመራሮች በአግባቡ አለመስራት ሳቢያ እጥረት የሌለባትን መሬትንና የሰው ሃብትን እንኳን በአግባቡ መጠቀም አልቻለችም። በእጅጉ የሚያስቆጭ ነው። ከማስቆጨት አልፎም ዋጋ እያስከፈለን ነው—ማንም ሰው የሚያጭደው የዘራውን ነውና። የየክልሉ አመራሮች ስራቸውን በአግባቡ ሳይሰሩ በቅረታቸው ጉዳዩን ለማስካከል ጥርጊያ መንገድ የማመቻቸት ሁኔታ በህዝባዊው መከላከያ ሰራዊታችንና በሌሎች የፀጥታ ሃይሎች ትከሻ ላይ ወድቋል።

የኢፌዴሪ ህገ መንግስት የህዝቦችን መሰረታዊ ጥቅሞች የደነገገ ነው። ህገ መንግስታችን በአንቀፅ 40 (3) ላይ እንደደነገገው፤ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ነው። ሀገራችን ከዚሁ ህገ መንግስት የመነጨ፣ ሊያሰራና የህዝቦችን ተጠቃሚነትን ሊያረጋግጥ የሚችል የመሬት ፖሊሲ አላት። ይህ ፖሊሲ መሬት የህዝብና የመንግስት መሆኑን በዝርዝር ያስረዳል። መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና የህዝቦች የጋራ ንብረት እንደሆነም ይተነትናል።

ርግጥ ነው— አዲሲቷ ኢትዮጵያ የመሬት ሃብታም እንጂ ድሃ አይደለችም። እንኳንስ ለእኛ ቀርቶ ለልማት አጋሮቻችንም ቢሆን የሚተርፍ ከሶስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ ጥቅም ላይ ያልዋለ መሬት እንዳለን ይታመናል። መሬት የህዝብና የመንግስት ሃብት በመሆኑ፤ መዋል የሚገባው ለስራና እና ለሃብት መፍጠሪያ ነው። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ይህ አልሆነም። ወጣቱ መሬት የማግኘት መብት ቢኖረውም ቅሉ፣ የሰጠው አካል የለም። ይህ ሁኔታም የገጠር ወጣቶችን ከመደናገር አልፎ ተስፋ እንዲቆርጡ ያደረጋቸው ይመስለኛል።

ርግጥ እነዚህ ችግሮች መሬት ላይ ያሉ ክስተቶች ናቸው። ክስተቶቹ እኛ ሀገር ብቻ ያሉ አይደሉም። የደረጃቸው ሁኔታ የሚለያይ ካልሆነ በስተቀር፣ ድህነትም ይሁን ስራ አጥነት የሁሉም ሀገራት ችግሮች ናቸው። ግና ችግሮቹ በሁሉም ሀገራት ውስጥ ስላሉ፤ በእኛ ሀገር ውስጥም የግድ መኖር አለባቸው እያልኩ አለመሆኑ ሊታወቅልኝ ይገባል። የእኛ ሀገር ሁኔታ ለየት ያለ ነው እያልኩ እንጂ። ምንም እንኳን ችግሮቹ የሚያደናግሩና ተስፋ የሚያስቆርጡ ቢመስሉም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ችግሮቹን የመፍታት አቅምም ይሁን ብቃት አለው። ትናንት ዜሮ በጀት የነበራትን ሀገር ተረክቦ፣ ዛሬ ቢሊዮኖችን መድቦ በልማት ጎዳና የገሰገሰ፣ በአሳፋሪ ድህነት ውስጥ የነበሩ ዜጎቿን ህይወት ቀይሮ ለአፍሪካዊያን ወንድሞቻችን የዕድገትና የለውጥ ተምሳሌ የሆነና ሌሎች ህልቆ

መሳፍርት የሆኑ ተግባራትን የፈፀመ መንግስት ወጣቶች ያሉባቸውን ጊዜያዊ ችግሮች አይፈታም ተብሎ አይታሰብም። ችግሮቹ መንግስት እስካሁን ካለፉቸው ተግዳሮቶች አኳያ ሲታዩ የሚያደናግሩና ተስፋ የሚያስቆርጡ አይደሉም።

ርግጥ የሀገራችን ወጣቶች መፃዒ ተስፋ ስርዓታቸው ብቻ ነው። ሌላ ከማንም አይደለም። እናም መደናገርና ተስፋ መቁረጥ የስርዓቱ ወጣቶች ባህሪ ሊሆን አይገባም። ስለሆነም ተደናግሮ ተስፋ ቆርጦ አመፅን እየተለማመደ ያለው ወጣት የመጪው ጊዜ ተስፋውን ማጨለም አይኖርበትም። መንግስት ቀደም ባሉት ጊዜያት በአገሪቱ ውስጥ ድህነትን አቅም በፈቀደ መጠን በመቀነስ ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ እንደሚደርግ፤ ትምህርትን፣ ጤናን፣ የመሰረተ-ልማት አውታሮችን እንደሚያስፋፋ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ ስር እንዲሰድ አደርጋለሁ በማለት የገባውን የተስፋ ቃል ተፈፃሚ ማድረጉ ከወጣቱ የሚሰወር አይደለም። አስተማማኝ ሰላም በማረጋገጥ ረገድም የገባውን ቃል አላጠፈም። ነገም ይሁን ከነገ ወዲያ ይህን ህዝባዊ ተግባሩን ይፈፅማል። ይህም የወጣቱን ተስፋ የሚያለመልም እንጂ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም።

ያም ሆኖ ወጣቱ ስርዓቱ የእርሱ እንደ መሆኑ መጠን ሊጠብቀው ይገባል። በተለያዩ ጊዜያት ብቅ ጥልም እያሉ በየአካባቢው የሚታዩ ግጭቶች መነሻቸውና መድረሻቸው ስርዓቱን በውል ካለመገንዘብ አሊያም የግል ጥቅማቸውን ለማሳደድ በሚሹ ነውጠኞችና ፀረ ሰላም ሃይሎች አማካኝነት የሚነሱ ናቸው። እነዚህን ሃይሎች እንደ አመጣጣቸው በመመለስ አደብ ለማስገዛት መንግስት ማናቸውንም ተግባሮች እንደሚከውን ቃል ገብቷል። ታዲያ ወጣቱ የማናቸውም ችግሮች መፍትሔ የሚመነጨው በሀገሪቱ ህዝብ አመኔታ ከተመረጠው መንግስት እንጂ የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ለማራመድ ብሎም የሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ተላላኪ በመሆን በቀለም አብዮት በህዝቦች ስቃይ ትርፍ ለማጋበስ በሚፈልጉ ሃይሎች አለመሆናቸውን ማወቅ አለበት።

ስለሆነም መንግስት የአዳዲስ ልማታዊ ሃሳቦችና አሰራሮች አመንጪ ብሎም ለወጣቱ ችግር የሚደርስ ህዝባዊ አካል መሆኑን በመገንዘብ፤ ከእነዚህ ሃይሎች አሉባልታ በመራቅ የእነርሱ እኩይ ዓላማ መጠቀሚያ ላለመሆን መጠንቀቅ ይኖርበታል። ወጣቱ የመንግስትን የለውጥ ሃይልነት ስለሚያውቅ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጪ እንደማይወጣና እንደሚለወጥም ማመን አለበት። ከመሰንበቻው በኦሮሚያ ክልል ወጣቱ ከህዝባዊው መከላከያ ሰራዊታችን ጋር እያደረገ ያለው ውይይት የዚህ አባባሌ አስረጅ ነው።

በውይይቱ ወጣቱ መሳሳቱንና ሲፈፅመው የመጣው ተግባር እንደፀፀተው መገንዘቡ ችግሩ የሚፈታበትን ሁኔታ ያመላከተ ይመስለኛል።

አዎ! የወጣቱ ተስፋ ልማት ነው። አጀንዳው ስራ ማግኘት ነው። አመፅና ሁከት የእርሱ አጀንዳዎች አይደሉም። ባለቤቶቹ ሌሎች ናቸው። እናም የራሱን ተስፋ ትቶ የሌሎች መጠቀሚያ መሆን የለበትም። በአመፅና በሁከት ተጎጂው እርሱ ነው። የአጀንዳዎቹ ባለቤቶችና አነሳሾች ባህር ማዶ ሆነው እርሱን ፍም እሳት ላይ እየማገዱት እነርሱ ቀይ ውስኪያቸውን ይጎነጫሉ። እናም ወጣቱ ከእነዚህ ሴረኞች አጀንዳ ራሱን ማላቀቅ ይኖርበታል። ርግጥ ይህ 'ወጣቱ ከሴረኞች አጀንዳ እንዴት ነፃ ይውጣ?' የሚለው ጉዳይ ራሱን የቻለ አጀንዳ ነው። እናም በዚህ ዙሪያ ያለኝን ሃሳብ ለማካፈል ሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ። ለዛሬው ግን ወጣቱ መንግስት ችግሮቹን እንደሚፈታ በማመን ራሱን ከአመፃ ተግባር ሊያቅብ እንደሚገባ የማስገነዝበው ስሜቱና ፍላጎቱ ተመሳሳይና ቅርብ እንደሆነ ዜጋ ጭምር ነው።